ፓኖራማ 44

የትዝብት አድማስ

መስከረም 23 ቀን 2001 ዓም

## የወራት መፈራረቅ የእስስትን ቆዳና ባኅርይ አይለውጠውም

በአንድ ዓመት ውስጥ የተካተቱት ወራት ወቅታቸውን እየጠበቁ መለዋወጣቸው የተፈ ጥሮ ህግ ነው:: መጸው ለበጋ፥ በጋው ለፀደይ፥ ፀደዩ ለክረምት፥ የተፈጥሮን ሕግ በማ ክበር፥ ተራቸውን እየጠበቁ፥ቦታቸውን እየለቀቁ ይሄዳሉ:: ይመለሳሉ:: በዚያው መጠ ን፥ መልከዓ - ምድርም መልኩን ይለዋውጣል ፡ አዝርዕትና ዕፅዋዕትም እንደዚሁ የተ ፈጥሮ ህግ ተገዥዎች ናቸው:: ሌላው ቀርቶ ደንጋዩና ዛፉ ሳይቀር፥ ከዘመን ብዛት የተነሳ፥ ይሸብታል፥ ይወይባል:: መልኩን ይለውጣል:: ተፈጥሮ ሁሉ ጊዜ በማያቋርጥ እንቅስቃሴ ሂደት ውስጥ ስለሆነች፥ ለውጥ የነበረ፥ ያለና የሚኖር መሆኑ የተፈጥሮ ህግ ነው:: ይህን መሠረታዊ ሀቅ የማይቀበል፥ ተቀብሎም፥ እራሱን ለመለወጥ የማይዘ ጋጅ ሁሉ፥ እራሱንም እየለወጠ በተፈጥሮ የእንቅስቃሴ ሂደት ውስጥ ሰልፉን ካላስተካ ከለ፥ በተፈጥሮ የእንቅስቃሴ ሂደትና ፍጥነት ተጨፍልቆ ይቀራል:: አመድ-ትቢያም ይሆናል:: ይህም ሀቅ በዓለም ዙሪያ በነበሩ ሁኔታዎች በተደጋጋሚ የታየ ክስተት ነው:

እንዳጋጣሚ ሳይሆን፥ እንደ አለመታደል እንበለውና፥ ሀገራችን ከተፈጥሮ ጋር ያላት የለውጥ እንቅስቃሴ፥ እስከዛሬ ድረስ፥ የሰመረ፥ የተስተካከለና የተወዳጀ ሆኗል ለማለ ት የሚያስቸግር እየሆነ መምጣቱን ቀጥሏል:: ያማ ባይሆን ኖሮ፥ አሁን ካለችበት ሁኔ ታ በተሻለ ደረጃ ለመገኘት በቻለች ነበር:: በተለይም የሀገራችንን የገጠሩን ነዋሪ ዜጋ ሕይወት ለተገነዘበው፥ ተፈጥሮና እንቅስቃሴዋ በአንድ በኩል፥ ኢትዮጵያና ዜጎቿ በሌ ላ በኩል ሆነው፥ የጎሪጥ የሚተያዩ እንጅ፥ በአንድ ዓይነት የጉዞ አቅጣጫና የለውጥ

እንቅስቃሴ ላይ የሚገኙ በሆኑ ነበር:: አስተውሎ ለአያቸው፥ ዓለምና ኢትዮጵያ ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ የሚሄዱ ነው የሚመስሉት:: ዓለም ወደፊት፥ ኢትዮጵያ የኋልዮሽ ማለት ነው:: ለዚህ ሁሉ እፀፅና ችግር ተጠያቂወቹ ግን፥ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ አይደ ሉም:: ዓይነተኛ ተጠያቂዎቹ፥ ሀገር እንመራለን የሚሉ ክፍሎች ናቸው:: የተማረው ክፍልም ከተጠያቂነትም ይሁን ከኃላፊነት ሊያመልጥ አይችልም:: እንደ አፈርሳታ ተካፋይ አንዱ ወገን፥ በሌላው ላይ ለማመካኘት ካለሆነ በስተቅር፥ በኢትዮጵያ መሠረ ታዊ ለውጥ ላለማምጣት ሁሉም የየድርሻውን ሚና ተጨውቷል ለማለት የሚያስችል ነው ቢባል ከዕውነት የራቀ አይደለም:::: ያ አርዕድ-አንቀጥቅጥ የነበረው የየካቲት 66 ሕዝባዊ አመፅ እንኳ ቢሆን፥ የኢትዮጵያን የዘመናት መከራና ችግር የሚለውጥ ለው ጥ ሳይሆን፥ የሕዝብን ዕልቂትና ጥፋት ያስከተለ ሁኔታን ፈጥሮ ነው የሄደው:: ይህም የሆነው ለውጡ እራሱ ያመጣው ጥፋት ሳይሆን፥ ለውጡ በአጥፊዎችና በመሀይሞች እጅ በመግባቱ ነበር:: ለቁጥር የሚሰለች የተማረ ዜጋ ወድሞ፥ የዛሬ ተስፋ ሊሆኑ የሚ ችሉ ወጣቶች ተጨፍጭፈው፥ ለሀገር የሚጠቅሙ አያሌ መካሪ አዛውንት ተረፍርፈው ፥ ወላጅ እናት ከል ለብሳና አንጀቷን አሳርራ፥ የወላድ መካን ሆና ቀርታ፥ ዛሬ ኢትዮ ጵያ ያገኘችውን ድል ሁሉ ቀልባሾች አባለሽተውት የሕዝቧ በጎሳ መከፋፈልን፥ ወደብ አልባ መሆንን፥ የሀገር መቆራረስን፥ የዜጎች መሰደድን፥ የሀገር ንብረት መመዝበርን ፥ የዓለም መሳቂያ መሳለቂያ መሆንን፥ ረሀብ- ድህነትን፥ በሽታን፥ መከራንና ሰቆቃን ያተረፈች ሀገር ሆና ቀርታለች::

የኢትዮጵያ ተራሮችና ሸንተረሮች፥ ሸለቆዎችና ሜዳዎች ፥ወንዞችና ዥረቶች ሁሉም በየፊናቸው የሚያንፀባርቁት የኢትዮጵያን ሰቆቃ እንጅ ደስታዋንና ሀሴቷን አይደለም :: በምዕራብ ኢትዮጵያ የነበረው ደንና ዛፍ እየተቆረጡ ወደ ሱዳን በመሄዱ አካባቢው በሚያስደነግጥ ፍጥነት ወደ ምድረ-በዳነት እየተለወጠ መሄዱን የዓይን ምስክሮች አን ጀታቸው እያረረ ይመሰክራሉ:: ኬንያ በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት በነበረችበት ወቅት ፥ዕል ፍ አዕላፍ እንስሳት፥ አውሬዎችና አዕዋፍም ከኢትዮጵያ በግድ ወደ ኬንያ እንዲሰደዱ ተደርገው ሳይመለሱ እንደቀሩት ሁሉ፥ ዛሬም፥ ተመሳሳይ ክስተት እየተካሄደ ነው:: ዛሬ ኢትዮጵያ እንኳን ዜጎቿ፥ እንስሳት ሁሉ ሳይቀር መሰደድን መርጠዋል:: ሞቴን

ሀገሬ ያድርገው የሚባለው ቀርቶ፥ ሕይወቴን በስደት መቃብሬን በኢትዮጵያ የሚባል
ፈሊጥ መጥቷል:: አንዳንዱማ ሀገራችን ጠፍታ ከጠፋች በኋላ መገልበጫውን ለማሳመ
ር ሲል፥ ነፈሰ-ጡር ሚስቱን አሜሪካ ሄዳ እንድትወለድ በመሽቀዳደም ለይ መሆኑ
በርካታ ታዛቢዎች በሀዘን ይናገራሉ:: ጠላቶቿ ኢትዮጵያን "ሲያል" ሲሏት የነበረቻው
ን ሀገር፥ ወደ ዕውነት እየለወጧት ይገኛሉ:: ሰማይ ጠቀስ ህንፃዎች ተገነቡና፥ የቀለበ
ት መንገድ ተሰራና፤ ወይም ደግሞ፥ የተወሰኑግለሰቦች የባለ ብዙ ሚሊዮን ሀብት
ባለቤቶች ሆኑና፥ ኢትዮጵያ ተለውጣለች ሊሉ የሚከጅሉ ከንቱ የከንቱ -ከንቱዎች
እንዳሉ ይነገራል:: ነገር ግን ለውጥ አድርጋለች በሚባልባት አዲስ አበባ ብቻ እንኳ፥
ዕልፍ አዕላፍ ዜጎች፥ የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ ያረረባቸው ምፅዋተኞች እንዳሉ
የሚመሰክሩበት ልሳን የላቸውም:: የድሎት ምሳሌ ነው ከሚባልልት የአዲስ አበባው
ሸራተን ሆቴል በጥቂት ርቀት በሚገኝ ቦታ ላይ ስንቱ ዜጋ መጠጊያ አጥቶ እንደሚቆ
ራመድ ግን ለማየት ቀርቶ ለመስማት እንኳን አይፈልጉም:: ለውጥ በኢትዮጵያ አለ
ከተባለ፥አዎንታዊ ሳይሆን አሉታዊ፥ ገንቢ ሳይሆን አጥፊ፥ ሕይወት ሳይሆን፥ ሞት፥
ወደፊት ሳይሆን የኋልዮሽ ነው:: እርግጥ የነባቢት ለውጥ እንደ አፈር ነው:: በመፈክር
ደረጃ፥ ከፍተኛ የቋንቋ ለውጥ አለ ማለት የሚቻል ይሆናል:: በደርግ ጊዜ የነበረው
የፕሮፓጋንዳ ቋንቋ፥ የጨረቃን እንጎቻ የሚያበላ፥ ዜጎችን በዕርጎ ባህር የሚያሰዋኝ፥
አንድ በርሜል ውሃን በአስር በርሜል ነዳጅ የሚለውጥ፥ ተፈጥሮን ተቆጣጥሮ፥ አብዮ
ቱን ከሰማየ -ሰማያት አሸጋግሮ፥ ምርቱ ተትረፍርፎ፥ ዜጎቹ ሁሉ በልተው ተመግበው
፥ እንደነበሩ የሚያደነቁር ውሸትና ቅጥፈት ነበር:: የደርጉ መሪ ሳይቀር፥ የመጨረሻዋ
ን ጥይት ጠጥቼ የቴዎድሮስን ታሪክ እደግማለሁ ሲል እንደነበረ ሁሉም የሚያወቀው
ነው:: ያደረገው ግን፥ ሀገርን በትኖ ሠራዊቱን አጋልጦ ሕዝቡን ይቅርና ጓደኞቹን ከድ
ቶ እንደ ነጋበት ጅብ መፈርጠጥ ነበር:: ነባቢትና ድርጊት በጣም በጣም የተለያዩ ነገ
ሮች ናቸው:: ዛሬ ደግሞ በወያኔ ቋንቋው ተለውጧል:: በሀገሪቱ ዛሬ፥ የብሔሮች እኩ
ልነት ሰፍኖ፥ ዴሞክራሲ መጥቶ፥ የሰብዓዊ መብቶች ተከብረው፥ ረሀብና ብሽታ በቁ
ጥጥር ስር ውለው፥ ፍትህ ርትዕ ነግሠው፥ ሰላምና መረጋጋት ተገኝተው እንዳሉ ተደር
ጎ ይነገራል:: ነባቢትና ድርጊት፥ የሰማይና የምድር ያኅል ርቀት እንዳላቸው ግን አይ
ገነዘቡትም:: የወሬ የለው ፍሬ የአበባ የለው ገለባ ተብሏል ድሮውንም! የደርግ ዓብዮት
ቋንቋና የወያኔ የብሂር ቋንቋ አንድ አምሳል አንድ አካል በመሆናቸው፥ የቋንቋው ለ

EthioLion.com

ውጥ እምብዛም ያመጣው ለውጥ የለም:: ቋንቋን ቢለዋውጡት ደግሞ ለሕዝብ የሚጠቅም ፋይዳ አይኖረውም::

የሀገራችን መሪዎች ነን ባዮች፥ ዘመን የማይለውጣቸው፥ ታሪክ የማያስተምራቸው፥ ተመክሮ የማያሻሽላቸው፥ የሕዝብ እሮሮ የማይሰማቸውና የሀገሪቱ መከራም የማይፀፀታቸው ናቸው:: ይልቁንም፥ ሥልጣን የሚያሳብዳቸው፥ የሕዝብ ጥያቄ የሚያስበረግጋቸው፥ የመንግሥት ወንበር የሚያደነዝዛቸው፥ የተቃዋሚዎች መሰባሰብ የሚያርበተብታቸው በአንፃሩ ደግሞ፥ የባዕዳን ከንቱ ውዳሴና ባዶ ሙገሳ የሚያፍነከንካቸው ናቸው:: ይኽ ባህርይ ደግሞ የመሪዎች ባኅርይ ሊሆን አይገባው ነበር:: አብሶማ የወያኔ መሪዎች ባኅርይና ተግባር፥ ለመሪዎች ሊሰጥ በሚያስችል መስፈርትና ቁና ቢለካ፥ እጅግ አድርጎ የሚያዋርዳቸውና ሀገሪቱንም የሚያሳፍራት ነው:: በመሪነት ደረጃ ቀርቶ፥ ማንኛው ባተሌ ዜጋ እንኳ ሊዋሸው የሚቀፈውን ተራ ውሸት ከመዋሸት አንስቶ፥ ዛሬ የተናገሩትን ነገ ከመካድ ጀምሮ ያለውን ቅጥፈት ሲናገሩ፥ ትንሽም ቢሆን የማይቀፋቸው ግለሰቦች የተጠራቀሙበት የወያኔ ድርጅታቸው ምን ዓይነት መርኃ-ግብርና ሥነምግባር ይዞ እንደሚሄድ ያስገርማል:: ጫካ በነበሩበት ጊዜ የነበራቸውን አሳፋሪ ታሪክ እንኳ ለጊዜው ወደጎን ትተን፥ ከምኒልክ ግቢ ከገበቡት ከአለፉት አስራ ሰባት ዓመታት ጀምሮ የሚያደርጉትንና የሚናገሩትን እንኳን ብንታዘብ፥ የወያኔ መሪዎችና እስስት የምትባለው አነስተኛ ፍጡር ተመሳሳይ መሆናቸውን መገንዘብ አያዳግትም:: የእስስትን በየጊዜው የመልክና የባኅርይ መለዋወጥ ተገንዝበን ይህ ለምን ሆነ በማለት የተፈጥሮን ምሥጢር ለመመራመር ስንል ጊዜያችንን ማጥፋት አይኖርብንም:: እስስትን ለማወቅ፥ የወያኔን ማንነት ብቻ መከታተል ይበቃል:: የእስስትን ማንነት ለማወቅ ደግሞ፥ ላቦራቷር ውስጥ ወይም የምርመራ ቦታ መግባት የለብንም:: ይህ ተግባር በሙያው የሠለጠኑ የተፈጥሮ ተመራማሪዎች ድርሻ ነው የሚሆነው:: ወያኔ ግን፥ ሀገራችንን እያጠፋ፥ ሕዝባችንንም እየጎዳ ያለ ቡድን በመሆኑ፥ ድርጊቱንና ባኅርዩን በአርምሞ የምንመለከተው አይሆንም:: በኢትዮጵያ መንበረ-ሥልጣን ተፈናጥጦ እስከቆየ ድረስ፥ እየተከታተልን አካሄዱንና ተግባሩን ማጋለጣችን፥ ስውር ደባውንም ሆነ እንደ እስስት ተለዋዋጭና እኩይ ጠባዩን መዋጋታችንን እንቀጥልበታለን::

EthioLion.com

በዚህ በያዝነው አዲስ ዓመት በአዲስ ዘዴና ተንኮል ወያኔ የጀመረው አዲስ ሽብርና
መቅበዝበዝ ያለምክንያት አይደለም:: ከሁለት ዓመታት በኋላ ለማካሄድ ላቀደው የው
ሸት ምርጫ ከአሁኑ የቅድመ ዝግጅት መሰናዶ ይረዳኛል ብሎ በማሰብ ነው:: የሚቀጥ
ለውንም ምርጫ በግድ ማሸነፍ ይኖርብኛል ብሎ በመነሳቱ፥ አሁንም እንዳለፈው እሽ
ያለውን በማባበል፥ እምቢ የሚለውን ደግሞ በኃይልና በማስፈራራት እንዲመርጠው
ለማድረግ አስፈላጊውን ሁሉ የቤት ሥራ ከአሁኑ ተያይዞታል:: ይህንም በተግባር ለመ
ተርጎም፥ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ከሚገኙ ሰፈርተኞች ጀምሮ እስከ አዲስ አበባ ቀበሌዎ
ች ድረስ፥ የራሱን ደመዎዝተኛ ካድሬዎች ቀጥሮ ለማሰማራት ሰፊ ዕቅድ አለው:: ከት
ግሉ ጎራ እየተፈነጠሩ ለሚገቡለትም እርሱ በሚፈልገው ዕቅድ እያዘጋጀላቸው ይገኛል
:: እነኝህ የወያኔ ቅጥረኞችም፥ ምርጫውን በሚመለከት ልዩ ሥልጠናና መመሪያ ተሰ
ጥቷቸው ካሁኑ ለስምሪት የሚያበቃቸውን ሁሉ እያደረገላቸው ነው፡ ከተግባራቸው
መካከልም፥ የስለላና የክትትል ሥራ፥ የአካባባዊውን ነዋሪዎች መቆጣጠር፥ ተጠርጠሪ
ዎቹን ማስፈራራት አከባቢያቸውንም እየለቀቁ እንዲሄዱ ማስገደድ፥ በምትካቸውም
የወያኔን ታማኞች ማስገባት፥ በጥቅማ ጥቅም መደለል፥ የምርጫ ሳጥንን በመክፈት
የምርጫ ካርዶቹን ወደ ወያኔ ሳጥን መገልበጥ፥ በመራጩ ሕዝብ ዘንድ ብዥታን
መልቀቅ፥ የመሳሰሉትን ሁሉ ያጠቃልላል:: ወያኔዎች፥ በአንድ በኩል፥ ይህንን ዕኩይ
ና ፀረዴሞክራሲ ተግባር እያዘጋጁ፥ በሌላ በኩል ግን የዓለምአቀፍ ህብረተሰብን
ለማወናበድ፥ ደግሞ ካለፈው ተመክሯቸው በመነሳት የውጭ ታዛቢዎችን የሃሰት
ድጋፍ ለማግኘት፥ ካለፈው ጊዜ ለየት ባለ መልኩ በመዘጋጀት ላይ እደሆኑ ተደርሶባ
ቸዋል:: በወያኔዎቹ ቤት፥ ብልጥ ፖሊቲካ ማካሄዳቸው ሳይሆን አይቀርም::

በእኛ ዘንድ፥ በጣም የሚገርም ህቅ ባይሆንም እንኳ፥ የወያኔ የበላይ ጠባቂዎች፥ ወያኔ
ን፥ ሌላው ቢቀር፥ ከኬንያና ከዚምባብዌ የምርጫ ሂደት በመጠኑም ቢሆን ግንዛቤ
እንዲያገኝ አለመሞከራቸው ነው:: በአንድ አፍ ሁለት ምላስ ያለው የወያኔ አመራር፥
በፈለገው መንገድና ወደአሰኘው አቅጣጫ ሲገለባበጥ፥ሲለዋወጥ ምንም ዓይነት የኅሊና
ትዝብት ያለው አይደለም:: ሰብዕናን እየሸጡ መለዋወጥ ለውጥ ከሆነ፥ ወያኔያዊ ለው
ጥ እንጅ፥ ለኢትዮጵያ ለውጥ ሊሆን አይችልም:: ተፈጥሮን ተመክሮ እንደማይለውጠ
ው ሁሉ፥ የዘመናት መለዋወጥም የወያኔን ሰብዕናም ሆነ ባኅርይ አይለውጠውም::
ኢትዮጵያ ማለት አማራ ማለት ነው፤አማራ ደግሞ ጠላቴ ነው፤ የመጨረሻ ዓላማዬ

EthioLion.com

ደግሞ ነፃና ሪፐብሊክ ትግራይን መመስረት ነው ሲል የቆየው ወያኔ ድንገት ተለውጦ ኢትዮጵያዊ መሆን አይችልም። በፖለቲካ ሂደት፥ “ዘር ከልጓም ይስባል” ብለን መደ ምድም ባንከጅልም፥ የጣሊያኑ ባንዳ የልጅ ልጅ የሆነው መለስ ዜናዊ፥ በሀገር ወዳድ ነትና በኢትዮጵያ ሕዝብ አፍቃሪነት አይታማም። እንዲያው በደፈናው መለስ ዜናዊ አፍቃሪ ኢትዮጵያ ይሆናል ብሎ መጠበቁ፥ “ግመል በመርፌ ቀዳዳ ያልፋል” ከማለት ጋር አንድ ነው።

እስስት ይቀያየራል-- ግን እስስትነቱ ያለ ነው። ወያኔ ቋንቋውና ነባቢቱ ሊለወጥ ይች ል ይሆን ይሆናል፥ ግን ፀረ ኢትዮጵያነቱ ዘለዓለማዊ ነው። ለዚህም ነው፥ ከእነግሳንግ ሱ ጠርጎ ጠራርጎ ማስወገድ የግድ የሚሆነው።

EthioLion.Com